# ስማችን --- ኢወክንድ
# ልሳናችን---- ነቅንቅ

**ልዩ ዕትም** **ሰኔ 2002 ዓ.ም**

## የኢሕአፓ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ) የአንደኛ ጉባዔና የምስረታ በዓሉን በተሳካ ሁኔታ አከናወነ

በሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገ የምስረታ በዓል የተወለደው ኢወክንድ የመጀመሪያውን ጉባዔ በካሊፎርኒያ ግዛት በሳንሆዜ ከተማ በሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ አካሂዷል።

በሰሜን አሜሪካ ከተለያዩ ከተሞችና ከካናዳ ከተሞች የመጡ ተወካይ አባሎች የተገኙበት ይህ አንደኛ ጉባዔ በተለያዩ አገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ግልጽ ውይይት የተካሄደበት ከመሆኑም በላይ በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ግንዛቤ የተገኘበትና የወደፊቱን የትግል አቅጣጫና ስልት ያመላከተ ጉባዔ ነበር ።

በዚህ የመጀመሪያው ጉባዔው ኢወክንድ ያለፈውን የአንድ አመት ጉዞ ዞር ብሎ የመረመረበትና የገመገመበት ከመሆኑም በላይ ለገጠሙ ችግሮችና ለተከሰቱ ድክመቶች ተገቢ መፍትሄ በመስጠት ጉባዔው እርምጃ የወሰደ ሲሆን ነባሩ የኢወክንድ አመራር በአጭር ጊዜ ውስጥ ያከናወናቸውን መልካም ተግባሮችን በአንክሮ አጢኖ የድርጅቱ ጠንካራ ጎኖች በይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መመሪያ ሰጥቷል።

ማዕከሉን አገር ቤት በማድረግ ኢወክንድ በአጎራባች ሀገሮችና እንዲሁም በተለያዩ አህጉሮች ቅርንጫፎችን በማቋቋምና አካሎች በመመስረት ድርጅታዊ አቋሙን በከፍተኛ ድረጃ ያጠናከረ ሲሆን ከቅርንጫፍ አካሎች ጋር የሚደረገው የስራ ግንኙነትና ትስስር ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጉባዔው አዳዲስ የአሰራር ስልቶች ቀይሷል። የሀገር ነቀርሳ የሆነውን ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ሁለ ገብ ትግል ሕዝባዊ አላማ ያላቸው ድርጅቶች የትግል ትብብር እንዲያደርጉ ጉባዔው ጥሪውን አስተላልፏል። በቀጣዩ የትግል ዘመን ለኢወክንድ የተቀላጠፈ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ የአመራር አባላትን በመምረጥ ጉባዔው ተጠናቋል።

በጉባዔው ማግስት ሰኔ 24 ቀን በሳንሆዜ ከተማ የኢወክንድ የመጀመሪያ በዓል ለማክበር የደመቀ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሂዷል። በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ በሳንሆዜ ከተማ ነዋሪ የሆኑና ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያንና እንዲሁም የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የተገኙበት ሲሆን የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት ጓድ እያሱ አለማየሁና ጓድ ፋሲካ በለጠ፤ ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ እንዲሁም የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ሊቀ መንበር ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ አየለ ንግግር አድርገዋል። ስለ ኢወክንድ አመሠራረትና አላማ ገላጭ የሆነውና በሀገር ፍቅር የነደደው ጽሁፍ በወጣት ሳሚ የተነበበ ከመሆኑም በላይ በተደጋጋሚ የተደመጠው የወጣት ሄኖክ ስነ ግጥም የቤቱን ስሜት በደስታና በፍቅር በኩራት አሙቆታል። ከተላያዩ የወክንድ ቅርንጫፍ አካሎችና ከወክንድ ደጋፊዎች የተላኩ የደስታ መግለጫ መልእክቶችም ተነበዋል።

ኢወክንድ የቀደሙ የጀግኖች አያቶቹን ታሪክ ፈለግ ተከታይ መሆኑን ለመግለጽ በእለቱ በህመም ምክንያት በሥፍራው ባይገኙም ሁለት ታላላቅ አርበኞች -ኮሎኔል አስናቀ እንግዳና ኮለኔል እምሩ ወንዴ- ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት አስተዋጾኦ በወጣት ታዘብው አስፋ ወኔ የተሞላው ንግግር ቀርቦ የትግል የምስክር ወረቀት በበዓሉ ላይ ተበርክቶላቸዋል።

በመጨረሻም ከ 40 አመት በላይ በትግል ውስጥ የቆዩት ጓድ እያሱ አለማየሁ ለወጣት ታዘበው አስፋ የኢትዮጵያ ስንደቅ አላማን ያስረከቡ ሲሆን ጓድ ፋሲካ በለጠ ደግሞ ለወጣት ሳሚ የኢሕአፓና አርማ አስረክበዋል። ለዘመናት(የትግሉ ነው ህይወቱ) የተባለው የኢሕአፓ የትግል መዝሙር ተዘምሮ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል።